# ምንድ ነው እሱ ችኮላው

ንጋቱ ያየህይራድ

የቆምክባት መሬት ከድታ አለት የመሰለው ተንዶ ፣
ይፈራ የነበረው ሰውነት  ፈርቶ ተንሸራቶ  ቁልቁል ወርዶ፣
ለተነገረው አባታዊ ቃል  ለማይቀር  ሞት አካልህ ሰግዶ፣
አሳርፈኝ አለ ገላህ ዛሬስ ዘላለማዊ እረፍት ወዶ።

የአምስት ዓመት ያስር ዓመት ንድፈ እቅድ ስታሰላ፣
መንገድ ስታስመነጥር የወንዝ ደለል ስትሞላ፣
ግድብ ስታስገነባ ኩራዝ በመብራት ስትተካ፣
ትምህርት ቤት ስታሰራ የርሻ መሬት ስታስለካ፣
መታመምን ዘንግተሃል ሞትን እረስተህ ነበር ለካ።

የሰው እውቀት የሚለካው በስራው በልሳኑ እንዲሉ፣
የሚስማሙህ ሳይሆኑ የሚጠሉህ በጉብዝናህ ይስማማሉ፣

መች አለቀሱ ጓደኞችህ ለታጋይ አይለቀስም ብለው፣
የጀመርከውን ሊቀጥሉ ተሰብስበው ተማምለው፣
መች አዘኑ የምታውቃቸው ማዘን ታሪክ ላልሰራ ብለው።

ምንድነው እሱ ችኮላው ዓባይ ተገንብቶ ሳይፎክር፣
የአፍሪካ  አቤቱታ ሳይዳረስ የተጀመረው ሃዲድ ሳይሰምር።

ምንድነው እኮ ችኮላው እረሃብ ሥራ አጥነት ሳይጠፉ፣
ድንቁርናና ታሪክ ሳይሆን ጅምር  ውጥኑ ሳይገፉ፥

እኮ እንዴት ጎበዝ ይወድቃል ጥይት ቦምብ ሳይመታው ከርሞ?
ጎበዝ እንዴት ይሸነፋል እንዴት ይወድቃል ታሞ።